የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 36
ADDIS ABABA - 12th May, 1998


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፻፲/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ...................................... ገጽ ፯፻፴፮


## CONTENTS


Proclamation No. 110/1998
Stamp Duty Proclamation ................................ Page 736


### አዋጅ ቁጥር ፻፲/፲፱፻፺

### ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ

በሰነዶች ላይ የተጣለው የቴምብር ቀረጥ የኪነጥበብ ዕድገትን፣ የፋይናንስ ተቋሞችን እንቅስቃሴ እና የካፒታል ንብረት ዝውውርን ለማገዝ በሚያስችል አኳኋን እንዲሻሻል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር ፻፲/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ግልግል" ማለት ስለግልግል፣ ስለዕርቅ፣ ስለስምምነት ወይም ስለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍርድ ቤት ሳይሆን በገላጋዮች አልቆ በጽሁፍ የተሰጠ ውሳኔ ነው፣

፪· "ማገቻ" የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ፣ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአምጪው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል፣

### PROCLAMATION NO. 110/1998
### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PAYMENT OF STAMP DUTY

WHEREAS, it has become necessary to amend the stamp duty levied on documents in a manner which would contribute to the development of art, the activities of financial institutions and the transfer of capital assets;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Stamp Duty Proclamation No. 110/1998."

2. *Definitions*

   In this Proclamation:

   1) "Award" means a decision in writing rendered by an arbitrator(s) on a reference made otherwise than by order of court in the course of suit by parties to a compromise, conciliation or arbitral submission or other similar matters;

   2) "Bond" includes any instrument, whereby a person obliges himself to pay money to another, on condition that the obligation shall be void, if a specific act is performed or is not performed, as the case may be; or any instrument attested to by a witness and not payable to order or bearer, whereby a person obliges himself to pay money to another;

፫· "የኅብረት ስምምነት" ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ የሠራተኞች ማኅበራት ወኪሎች እና በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ አሠሪዎች ወይም የአሠሪ ማኅበራት ወኪሎች ወይም አሠሪዎችን በሚወክሉ ተጠሪዎች መካከል ስለሥራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጽሁፍ የሠፈረ ስምምነት ነው፣

፬· "የሥራ ውል" ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው፣ በአሠሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመሥራት ሲስማማ በሁለቱ መካከል የሚመሠረት ውል ነው፤

፭· "ሰነድ" ማለት ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሠረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት፣ የተወገደበት፣ ልኩ የተወሰነበት ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ማንኛውም የጽሁፍ መረጃ ነው፣

፮· "ሚኒስትር" ማለት የገንዘብ ሚኒስትር ነው፤

፯· "ማረጋገጫ" ማለት የሕዝብ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ሰው በሰነዶች ላይ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፣

፰· "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማናቸውም ድርጅት ነው፤

፱· "ሰነድ ማስፈጸም" ማለት ሰነድ መስራት፣ ማውጣት፣ በሰነዱ የተመለከተውን ማስፈጸም ወይም ሰነዱን ማዛወር ነው፣

፲· "የመያዣ ሰነድ" ማለት ተበዳሪው ወይም ዋሱ ለአበዳሪ በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበት ሰነድ ነው፣

፲፩· "መተዳደሪያ ደንብ" እንደአግባብነቱ የመመስረቻ ጽሁፍን ይጨምራል።

፫· የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች

የሚከተሉት ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ ይከፈልባቸዋል፤

፩· የማንኛውም ንግድ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም የማንኛውም ዓይነት ማኅበር መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
፪· ግልግል፣
፫· ማገቻ፣
፬· የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ፤
፭· ውል፣ ስምምነትና የእነዚህ መግለጫ፤
፮· የመያዣ ሰነዶች፤
፯· የሕብረት ስምምነት፣
፰· የሥራ (ቅጥር) ውል፣
፱· የኪራይ፣ የተከራይ አከራይና መሰል መብት የማስተላለፊያ ሰነዶች ጭምር፣
፲· ማረጋገጫ፣
፲፩· የውክልና ሥልጣን፣
፲፪· የንብረት ባለቤትነትን ማስመዝገቢያ ሰነድ።

፬· የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ልክ

፩· በአንቀጽ ፫ ስር በተመለከተው በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ መከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ከዚህ ጋር በተያያዘውና የዚህ አዋጅ አንድ አካል ሆኖ በሚቆጠረው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተዘረዘረው ይሆናል።

፪· አንድ ሰነድ በተደጋጋሚ ተፈጻሚ ሲሆን ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው ነው።

3) "Collective Agreement" means an agreement relating to conditions of work, concluded in writing between one or more representatives of trade unions and one or more employers or agents or representatives of employers organizations;

4) "Contract of Employment" means an agreement formed where a person agrees, directly or indirectly, to perform, work for a definite or indefinite period or, piece work in return for remuneration;

5) "Instrument" means a written document by which any right or obligation is or purports to be created, recorded, transferred, extinguished or by which its scope is limited or extended;

6) "Minister" means the Minister of Finance;

7) "Notarial Act" means an act of attestation and certification performed by person(s) authorized to perform such acts;

8) "Person" means any natural person or any organization irrespective of having juridical personality;

9) "to Execute Instrument" means to draw, issue, to carry into effect or to negotiate an instrument;

10) "Security Deed" means any instrument whereby a borrower or guarantor gives to a lender a charge upon a part or the whole of his property;

11) "Articles of Association" include memorandum of association;

3. *Instruments Chargeable with Stamp Duty*

The following instruments shall be chargeable with stamp duty:

1) memorandum and articles of association of any business organization, cooperative or any other form of association;
2) award;
3) bonds;
4) warehouse bond;
5) contract and agreements and memoranda thereof;
6) security deeds;
7) collective agreement;
8) contract of employment;
9) lease, including sub-lease and transfer of similar rights;
10) notarial acts;
11) power of attorney;
12) documents of title to property.

4. *Rates of Stamp Duty*

1) The applicable rates of stamp duty for each instrument mentioned under Article 3 shall be those specified in the Schedule attached hereto and constituting an integral part hereof.

2) The rate payable at any subsequent execution of an instrument shall be as specified in the same Schedule.

፭· <u>የቀረጡ አተማመን</u>

፩· በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ መጠን በሠንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የዋጋው መቶኛ ይሆናል።

፪· በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል።

፫· አንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረጥ በብር ሳይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ፣ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው የምንዛሪ ልክ ነው።

፬· በስቶክ ወይም ሌላ ዋስትና ባለው ነገር ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ፣ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካኝ ዋጋ መሠረት ነው።

፭· ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለሉበት ወይም ለብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል።

፮· ሀ) ንብረትን በባለቤትነት ለማስመዝገብ በተቋቋመ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው።

ለ) በንብረቱ ሰነድ ላይ የተመለከተውን ዋጋ የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ ለዚሁ ጉዳይ የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ በሚሰይመው ኮሚቴ ይወሰናል።

፮· <u>የክፍያ ግዴታ</u>

፩· ከዚህ በታች በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት።

፪· በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱን የሚሠራው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ አለበት። ሆኖም አንድ ሰነድ የተሠራው ወይም የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰነዱን በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈጸመው ሰው ነው።

፫· በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኪራይ ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው።

፬· በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ ተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት።

፭· በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረቱ ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል።

5. *Mode of Valuation*

1) Where the value of the right or obligation executed by means of an instrument can be determined, the rate chargeable on such instrument shall be the percentage of such value as specified in the Schedule.

2) Where the value of the right or obligation executed by means of an instrument cannot be determined, the amount chargeable on such an instrument is the fixed amount specified for each such instrument in the Schedule.

3) Where an instrument is chargeable with stamp duty in respect of any amount expressed in any currency, other than Birr, such amount shall be computed on the basis of the prevailing rate of exchange.

4) Where an instrument is chargeable with stamp duty on an ad-valorem basis in respect of any stock or of any marketable security, such amount shall be computed on the average value of the stock or security prevailing at the time when the instrument is made.

5) Any instrument comprising or relating to several distinct matters shall be chargeable with the aggregate amount of duties payable in respect of each separate instrument.

6) (a) The stamp duty payable on documents tranferring title shall be calculated on the value of the property involved as agreed upon between the transferer and the transferee, provided however that such valuation is approved by the Federal Inland Revenue Authority;

(b) Where the value agreed between the transferer and the transferee is not acceptable to the Federal Inland Revenue Authority, the value of the property involved in the transfer of title shall, for the purpose of calculating the stamp duty, be determined by a special committee which shall be appointed for such purposes by the Federal Government Revenues Board.

6. *Liability*

1) Unless otherwise provided herein the beneficiary of an instrument shall be liable to pay the stamp duty thereon.

2) The person making (drawing) or issuing an instrument in Ethiopia shall, upon its execution, be liable for the payment of stamp duty; provided, however, that when an instrument is made (drawn) or issued outside Ethiopia the person who is first executing it in Ethiopia shall be liable for the payment of stamp duty.

3) Unless otherwise specified in the lease agreement the stamp duty in respect of the lease agreement shall be paid by the lessee.

4) The borrower shall be liable for the payment of stamp duty chargeable on security deeds.

5) The transferee shall, unless otherwise agreed, be liable for the payment of stamp duty chargeable on documents transferring title to property.

፮· ውል ወይም ስምምነት የሚመሰርቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

፯· በቅጥር ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሠሪው ይሆናል ።

፰· ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

፱· በኅብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሠሪውና ሠራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

፯· ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ

፩· የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በሚከተለው ጊዜና ሁኔታ ነው፤

ሀ) በመመስረቻና መተዳደሪያ ጽሑፎች፣ ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ፣

ለ) በግልግል ፣ ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ፣

ሐ) በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ፣ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈረሙበት ጊዜ፣

መ) በኪራይ ወይም በተከራይ አከራይ ውል ላይ ፣ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፣

ሠ) በማረጋገጫ ሰነድ ላይ፣ ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ፣

ረ) በመያዣ ሰነድ ላይ፣ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፣

ሰ) በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ፣ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ።

፪· ሀ) የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር ፶ በታች በሚሆንበት ጊዜ፣ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈጸማል።

ለ) የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር ፶ የበለጠ ሲሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ፣ የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል።

፫· ሀ) የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ የሚሠራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚሁ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሠራ መሠረዝ አለበት።

ለ) ቴምብር የተለጠፈበትን ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሰራረዝ የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በሚወስነው መሠረት ይፈጽማሉ።

ሐ) በሰነድ ላይ የተለጠፈ ቴምብር የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በሚወስነው መሠረት ካልተሠረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጠራል። በዚሁ ምክንያት የሚመጣው ኃላፊነት የሚወድቀው በባለጉዳዩ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሠራ ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ይሆናል።

፰· የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ሥልጣን

የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን፤

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን ቀረጥ ለመሰብሰብና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም፣

፪· ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ መዛግብትንና ደብተሮችን፣ ወረቀቶችን፣ ማናቸውንም ልዩ ልዩ ሰነዶችንና ውሳኔዎች እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እራሱ ቀርቦ እንዲያስመረምር ወይም እንዲያስረዳ ለማዘዝ፤

6) Parties to a contract or to an agreement are jointly and severally liable for the payment of stamp duty thereon.

7) The employer shall be liable for the payment of stamp duty on contracts of employment.

8) Parties to an award are jointly and severally liable for the payment of stamp duty thereon.

9) The employer and employees are jointly and severally liable for the payment of stamp duty on collective agreement.

7. *Time and Manner of Payment*

1) The stamp duty shall be paid:

(a) on memorandum and articles of association, before or at the time of registration;

(b) on awards, before or at the time of issuance of the award;

(c) on contracts or agreements, before or at the time of signature;

(d) on leases or sub-leases, before or at the time of signature;

(e) on notarial acts, at the time of issuance;

(f) on security deeds, before or at the time of signature;

(g) on documents of title to property, before or at the time issuance is effected.

2) (a) The payment of a stamp duty under Birr 50 shall be effected by affixing stamp of appropriate value to the instrument.

(b) When the stamp duty exceeds Birr 50 or where the type and nature of instrument so requires, the Federal Government Revenues Board may by directive provide that stamp duty be paid by means other than affixing stamp.

3) (a) Whoever executes or receives an instrument bearing an adhesive stamp shall at the time of execution cancel the same, so that it cannot be used again.

(b) Persons required to cancel the adhesive stamp shall cancel it in such manner as will be prescribed by the Federal Inland Revenue Authority.

(c) Any instrument bearing an adhesive stamp which has not been canceled as prescribed by the Federal Inland Revenue Authority shall be deemed, so far as such stamp is concerned, to be unstamped. The responsibility arising from the non cancellation of the stamp shall be on the person executing or receving the instrument bearing an adhesive stamp and not on the person submitting the document for execution.

8. *Power of the Federal Inland Revenue Authority*

The Federal Inland Revenue Authority is hereby vested with powers to:

1) collect the stamp duty determined under, and implement the provisions of this Proclamation;

2) require persons liable to pay stamp duty to submit for its inspection any registers and books, papers, documents and proceedings necessary for the determination of stamp duty, or where necessary to require the attendance of such persons who shall give the necessary explanation in the course of its inspection of such records;

፫· ጉዳዩ የሚመለከተው ቀረጥ ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሳይሆን በቀረ ጊዜ ቀረጡን በግምት ለመወሰንና ለመሰብሰብ ፡

ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፱· ይግባኝ የማቅረብ መብት

የፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በወሰነው የቴምብር ቀረጥ ሒሳብ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ባለሥልጣኑ ውሳኔውን በጽሑፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ ከ፳፩ ቀኖች በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

፲· የቴምብር ቀረጥ አለመከፈል የሚያስከትለው ውጤት

፩· ማንኛውም ሰነድ በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በሕግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፣ ምልክት አይደረግበትም ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶችን አይመለከትም።

፫· በዚህ አዋጅ መሠረት በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከ፲ ብር ማነስ የለበትም።

፬· ከዚህ በላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች የተወሰነው ቅጣት ተፈጻሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ከመከሰስ አያግድም።

፲፩· ከቀረጥ ነፃ መሆን

፩· ሚኒስትሩ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ከቴምብር ቀረጥ ነፃ ሊያደርግ ይችላል።

፪· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፹፱ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ናቸው።

፫· የአስመጪነት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚያስመጡት ንብረት በአስመጪዎቹ ስም በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም።

፬· መንግሥት ባጸደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሠረት ሰነዶች ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ።

፭· ተመሳሳይ መብት የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ኤምባሲዎችን፣ ቆንስላዎችን፣ እና ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን ሚኒስትሩ ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊያደርጋቸው ይችላል።

፮· የአክሲዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም።

፲፪· ቅጣት

፩· ማንኛውም ሰው፡

ሀ) ማናቸውንም ቀረጥ ሊከፈልበት የሚገባውን ሰነድ ተገቢው ቴምብር ሳይለጠፍበት ያስፈጸመ ወይም ከምስክርነት በስተቀር የፈረመ እንደሆነ፣

ለ) ተገቢውን ቀረጥ እንዳይከፍል ለማድረግ በማሰብ የአንድን ሰነድ እውነተኛ ሁኔታ የደበቀ እንደሆነ፣

ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፳፭ሺህ በማያንስና ከብር ፴፭ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ፲ ዓመት በማያንስና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

3) to determine by estimation and collect the stamp duty payable under this Proclamation if the concerned person fails to comply with its requests provided in Sub-Article (2) of this Article.

9. *Right to Appeal*

Persons dissatisfied with the decision of the Federal Inland Revenue Authority in respect of the amount of stamp Duty may, within 21 days from the date of notification of the decision rendered in writing, make an appeal against the decision to the Federal High Court.

10. *Effect of Non-payment of Stamp Duty*

1) No instrument chargeable with stamp duty shall be admitted in evidence for any purpose by any person having, by law or consent of parties, authority to receive evidence or shall be noted upon or authenticated by any such person or public office, unless such instrument is duly stamped.
2) Sub-Article (1) of this Article shall not affect the validity of the instrument when submitted as evidence in any proceedings in a criminal court.
3) Any instrument inadmissible in evidence in accordance with this Proclamation shall be admitted in evidence on payment of two times the amount due which shall not be less than 10 Birr.
4) The application of any penalty pursuant to the foregoing Articles shall not bar the prosecution of any person in accordance with Article 12 of this Proclamation.

11. *Exemptions*

1) The Minister may for good cause grant exemption from payment of stamp duty.
2) Public bodies on which the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 57/1996 applies shall be exempt from payment of stamp duties.
3) Goods imported for sale by traders having import license shall be exempt from payment of stamp duty when first registered in the name of the trader.
4) Documents may be exempted from the payment of stamp duty in accordance with international agreements and conventions approved by the Government.
5) Subject to reciprocity, the Minister may grant embassies, consulates and missions of foreign states exemption from payment of stamp duty.
6) Share Certificates shall be exempt from stamp duty payable on the register of title of property.

12. *Penalty*

1) Any person:
   (a) executing or signing, otherwise than as a witness, a document chargeable with stamp duty without the same being stamped;
   (b) who, with intent to defraud the appropriate payment of duty, conceals facts bearing on the true nature of any instrument;

shall be liable on conviction to a fine not less than Birr 25,000 and not exceeding Birr 35,000 and to rigorous imprisonment for a term not less than 10 years and not more than 15 years.

፪· ማንኛውም ሰው፣

ሀ) ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ተፈቅዶለት በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን የጣሰ እንደሆነ ፣ ወይም

ለ/ ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ሳይፈቀድለት ፣ የሸጠ ወይም ለመሸጥ ያቀረበ እንደሆነ ፣

ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፭ ሺህ በማያንስና ከብር ፳ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ፭ ዓመት በማያንስና ከ፲ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል ።

፲፫· <u>የተሻረና ጸንቶ የሚቆይ ሕግ</u>

፩· የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፸፱ ዓ.ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።

፪· የቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር ፪፻፳፩/፲፱፻፶፩ ዓ.ም ድንጋጌዎች ይህን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ጸንተው ይቆያሉ።

፲፬· <u>መመሪያ</u>

የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፲፭· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት



2) Any Person who:

(a) appointed to sell stamps or stamped papers, disobeys Regulations issued under this Proclamation; or

(b) not so appointed, sells or offers for sale stamps or stamped papers;

shall be liable on conviction to a fine not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 20,000 and to rigorous imprisonment for a term not less than 5 years and not more than 10 years.

13. *Repeal and Savings*

1) The Stamp Duty Proclamation No, 334/1987 is hereby repealed and replaced by this Proclamation.

2) The provisions of the Stamp Duty Regulations No. 221/1959 shall remain in force insofar as they are not inconsistent with this Proclamation.

14. *Directives*

The Federal Government Revenues Board may issue directives for the proper implementation of this Proclamation.

15. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 12th day of May, 1998.

Done at Addis Ababa, this 12th day of May, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## የቴምብር ቀረጥ ታሪፍ ሠንጠረዥ

በሠነዶች ላይ የሚከፈል የቴምብር ቀረጥ የሚወሰነው ፣ የሚጠየቀውና የሚሰበሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው፤

| ተራ ቁጥር | የሠነዱ ዓይነት | የተወሰደ ስሌት መሠረት | የማስከፈያ ልክ |
|---|---|---|---|
| 1 | የማንኛውም የንግድ ሥራ፡ ወይም ማናቸውም ሌላ ማኅበር የተመሠረተበት መተዳደሪያ ደንብ ፡<br>ሀ) መጀመሪያ ሲፈጸም<br>ለ) በመለጠቅ ሲፈጸም | በቁርጥ<br>" | ብር 350<br>" 100 |
| 2 | የሕብረት ሥራ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ፡<br>ሀ) መጀመሪያ ሲፈጸም<br>ለ) በመለጠቅ ሲፈጸም | በቁርጥ<br>" | ብር 35<br>" 10 |
| 3 | ግልግል | በዋጋው | የሚተመን 1%<br>የማይተመን ብር 35 |
| 4 | ማገቻ (ቦንድ) | በዋጋው | 1% |
| 5 | የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሠነድ | በዋጋው | 1% |
| 6 | ውሎች ፡ ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው | በቁርጥ | ብር 5·00 |
| 7 | የመያዣ ሠነድ | በዋጋው | 1% |
| 8 | የሕብረት ስምምነት<br>ሀ) ሲመዘገብ<br>ለ)ሲሻሻል | በቁርጥ<br>" | ብር 350<br>ብር 100 |
| 9 | የቅጥር ውል ስምምነት | የአንድ ወር ደመወዝ | 1% |
| 10 | ኪራይ፡ የተከራይ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፊያ ሠነድ | በዋጋው | 0·5% |
| 11 | ማረጋገጫ | በቁርጥ | ብር 5·00 |
| 12 | የውክልና ሥልጣን | በቁርጥ | ብር 35·00 |
| 13 | የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ | በዋጋው | 2% |

## *SCHEDULE OF STAMP DUTY RATES*

The stamp duty on each instrument shall be charged, levied and collected at the following rates:

| | Instruments Chargeable with Stamp Duty | Basis of Valuation | Rates of Stamp Duty |
|---|---|---|---|
| 1 | Memorandum andArticles of Association of any business organizations, or any association:<br>(a) upon 1st execution<br>(b) upon any subsequent execution | flat<br>flat | Birr 350<br>Birr 100 |
| 2 | Memorandum and Articles of Association of cooperatives<br>(a) upon 1st execution<br>(b) upon any subsequent execution | flat<br>flat | Birr 35<br>Birr 10 |
| 3 | Award | on value | (a) with determinable value 1%<br>(b) with undeterminable value Birr 35 |
| 4 | Bonds | on value | 1% |
| 5 | Warehouse Bond | on vlaue | 1% |
| 6 | Contracts and agreements and memoranda thereof | flat | Birr 5 |
| 7 | Security Deeds | on value | 1% |
| 8 | Collective Agreement<br>(a) on 1st execution<br>(b) on any subsequent executon | flat<br>flat | Birr 350<br>Birr 100 |
| 9 | contract of employment | salary | 1% |
| 10 | Lease including sub-lease and transfer thereof | on value | 0.5% |
| 11 | Notarial act | flat | Birr 5 |
| 12 | Power of Attorney | flat | Birr 35 |
| 13 | Register title to property | on value | 2% |